# ማውጫ


መግቢያ ........ 1

ምዕራፍ ስድስት፡ ተረት ........ 2

ክፍል አንድ ፡ ማዳመጥ ........ 2

ክፍል ሁለት ፡ መናገር ........ 3

ክፍል ሶስት ፡ ማንበብ ........ 4

ክፍል አራት፡መፃፍ ........ 5

ምዕራፍ ሰበት፡ ቤተሰብን ማገዝ ........ 7

ክፍል አንድ ማዳመጥ ........ 7

ክፍል ሁለት መናገር ........ 9

ክፍል ሶስት ማንበብ ........ 10

ክፍል አራት መፃፍ ........ 12

ምዕራፍ ስምንት፡ ባህላዊ ሙዚቃ ........ 14

ክፍል አንድ ፡ ማዳመጥ ........ 14

ክፍል ሁለት መናገር ........ 15

ክፍል ሶስት፡ ማናበብ ........ 15

ክፍል አራት፡ መፃፍ ........ 16

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ወፎች ........ 18

ክፍል አንድ፡መናገር ........ 18

ክፍል ሁለት ማንበብ ........ 19

ክፍል ሶስት ፡ መፃፍ ........ 21

ምዕራፍ አስር ፡ መረጃ ማግኘት ........ 24

ክፍል አንድ ማዳመጥ ........ 24

ክፍል ሁለት ፡ መናገር ........ 25

ክፍል ሶስት፡ ማንበብ ........ 26

ክፍል አምስት፡ ሰዋሰው ........ 28

ዋቢ መፃህፍት ........ 31

ከምዕራፎቹ ለተመረጡ መልመጃዎች ናሙና መልሶች ........ 32

## መግቢያ

ይህ የመማሪያ ሞጁል በወቅቱ በአለም አቀፍ ደረጃ በተፈጠረው የኮሮና ቫይረስ /ኮቪድ19/ ተላላፊ በሽታ ምክንያት መንግስት በሀገራችን ውስጥ የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስ ሲባል ትምህርት ቤቶች በሽታውን መቆጣጠር እስኪቻል ድረስ ዝግ እንዲሆኑ በመወሰኑ ምክንያት ተማሪዎች በመደበኛው ፐሮግራም ትምህርታቸውን መከታታል ባለመቻላቸው በቤታቸው ሆነው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ታስቦ የተዘጋጅ የስድስተኛ ክፍል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ መማሪያ ሞጁል ነው፡፡

ይህ ሞጁል በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት እንዲማሩት ከተዘጋጁት የትምህርት ይዘቶች ተውጣጥቶ ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚያስችል መልኩ በአጭሩ የተዘጋጀ ሞጁል ሲሆን ከምእራፍ ስድስት እስከ ምእራፍ አስር አምስት ምዕራፎችን አጠቃሎ ይዟዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ ሞጁል የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች በሚሰጣቸው መመሪያ

መሰረት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት፡ ተረት

# የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ተረት ትናገራላችሁ የተረቱን መልእክት ትገልፃላችሁ ።
- ተረትና ስዕሎችን  በድርጊትና በጊዜ ቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ።
- ተረት ትፅፋላችሁ
- በአካል እንቅስቃሴ መልዕክት ታስተላልፋላችሁ።
- ጭውውት ታደርጋላችሁ። ከጭውውቱም ፍሬ ሀሳብ ታወጣላችሁ።

ተማሪዎች የምዕራፍ ስድስት ትምህርታችን ተረት በሚልርዕስ ላይ ያተኩራል። ለመሆኑ ተረት ምንድን ነው?የየራሳችሁንግምት እንደሰጣችሁ አምናለሁ። ስኪ እኔ ደግሞ የተረትን ምንነት በአጭሩ ልንገራችሁ።

ተረት በጣም ጥንታዊ የሆነ ሰዎች የደከመ አዕምሮኣቸውን ለማዝናናትና ትውልድን በስነምግባር ለመቅረፅ ሲጠቀሙበት የነበረና አሁንም ያለ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የስነቃል ዘርፍ ነው።

### ክፍል አንድ ፡ ማዳመጥ

ተማሪዎች አሁን የማዳመጥችሎታችሁንማዳበር እንድትችሎ አንድ ተግባር እንድታከናውኑ አቅርቤላችኋለሁ። የተሰጣችሁን ተግባር ካከናወናችሁ በኋላ የሚቀርቡናችሁን የማዳመጥ ጥያቄዎች ትመልሳላችሁ።

### ተግባር

ተማሪዎች ከቤተሰባችሁ አባላት አንጋፋ የሆነ ሰው ምረጡና ተረት እንዲያወራላችሁ ጠይቁ። ከዚያም እናንተ በሚገባ አዳምጡ ። የተወራላችሁን ተረት በሚገባ ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የተረቱ ርዕስ ምን ይባላል ?

2. በተረቱ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች/እንስሳት እነማን ናቸው?

3. ተረቱ ምን መልእክት ያስተላልፋል ?

## ክፍል ሁለት ፡ መናገር

ተማሪዎች አሁን መናገር ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉበት ተግባር እሰጣችኋለሁ። ታድያ ተግባሩን ስታከናውኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መጠቀም የለባችሁም። ምክንያቱም ይህን ተግባር የምናከናውነው በአማርኛ ቋንቋ መናግርን ችሎታ ለማዳበር ስለሆነ ነው።

ተግበር 1.

ለሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በቃል ስጡ

1. ካሁን በፊት የሰማችሁትነና የምታውቁትን ተረት በቅርባችሁ ላለ ሰው አውሩ።

2. ያወራችሁትን ተረት በድርጊትና በግዜ ቅደም ተከተል ተረቱን ላወራችሁለት ሰው ግለፁ።

3. በተረት ውስጥ ስለ ተጠቀሱት ነገሮች ስምና ሙያ በዝርዝር ተናገሩ።

ተግባር 2.

1. አንድ ርዕሰ ጉዳይ አንስታችሁ ከቤተሰባችሁ አባላት ጋር ጭውውት አድርጉ።

ጭውውቱን ስታደርጉ ሁሉም ሰው ስለጉዳዩ የሚያውቀውን ነግር እንድናገር መገፋፋት ይኖርባችኋል።

2. ከጭውውቱ በጉዳዩ ላይ የተነሱ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻችሁ ከያዛችሁ በኋላ ፍሬ ሀሳቡን ብቻ ደግማችሁ ከተናገራችሁ በኋላ በጭውውቱ ላይ የተሳተፉትን የቤተሰባችሁን አባላት አመስግናችሁ አጠናቁ።

## ክፍል ሶስት ፡ ማንበብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የማንበብ ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉበት ምንባብ አቅርቤላችኋለሁ። ምንባቡን ለማንበብ ምቹ ቦታ ምረጡ። ሀሳባችሁን ሰብስባችሁ ልታነቡ የምትችሉበት የሚረብሻችሁ ድምፅ የሌለበት ቦታ ይሁን። ከዚያም ምንባቡን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ አንበብቡት። የምንባቡን ሀሳብ በትክክል መረዳታችሁን እርግጠኞች ስትሆኑ ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን የምትመዝኑበትን ጥያቄዎች በትእዛዙ መሰረት ለመስራት ሞክሩ፡

### አይጥና ድመት

ከእለታት አንድ ቀን ድመቶች ሴት ልጃሁን ለልጃችን ስጡን እንጋባ እንዛመድ ሲሉ ወደ አይጦች ቤት አማላጅ ላኩና አይጦችም በሀሳቡ ተስማሙና ሴት ልጃቸውን ለድመቶች ወንድ ልጅ ሊያጋቡና ሊዛመዱ ተስማምተው ውል ተፈራረሙ።

ከሰርጉ ቀን በፊት ከአይጦች አንዲቱ አይጦችን በሙሉ ሰብስባ እንዲህ ስትል መከረቻቸው። ድመት ምንም ሳንበድለው ለብዙ ዘመናት እያጠፋን መኖሩን ታወቃላችሁ። ዛሬ እንጋባ እንዛመድ የሚለን ሊያታልለንና ሊያጠቃን ቢሆንስ ማን ያውቃል? ስለዚህ ኑ ሁላችን ጉድጓድ እናማስ በሰላም ከመጡ በሰላም እንመልሳቸዋለን ለክፋት ከመጡ ግን ባዘጋጀነው ጉድጓድ ገብተን እናመልጣቸዋለን አለቻቸው። ሁሉም በዚህ ሀሳብ ተስማምተው ጉድጓድ ምሰው ሰርገኞቹን ሲጠብቁ ሰርገኛው ድመት "ሆ እንቅ እንቅ" እያለ ባጀብ ሲመጣ ሰምተው እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል ጥልቅ ጥልቅ በማለት ወደ አዘጋጁት ጉድጓድ ገብተው አመለጡ ።

መልመጃ አንድ

ሀ. ምንባቡን በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ድመት ወደ አይጦች ዘንድ የመጣው ለምንድን ነው?
2. ወገኖችዋን ሰብስባ የመከረች ማን ነች?
3. ድመት ከአይጦች ጋር ዝምድና የፈለገው ለምንድን ነው?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ

1. ድመት ወደ አይጦች የመጣው ዝምድናን በመፍጠር አብሮ ለመኖር ነው፡፡
2. በተረቱ ውስጥ የተጠቀሱት ባለታሪኮች አንበሳና ነብር ናቸው፡፡
3. ተረት በማንኛውም የዕድሜ ክልል ያለን ሰው ያስደስታል፡፡
4. ተረት ግዜን ለማሳለፊያ እንጅ ሌላ ምንም መልእክት አያስተላልፍም፡፡

መልመጃ ሁለት

ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቻቸውን ስጡ፡፡

1. መማስ
2. መምከር
3. መዛመድ
4. ማታለል
5. መበደል

## ክፍል አራት፡መፃፍ

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከላይ ባነበባችሁት ተረት ውስጥ በድርጊት ተሳታፊ የነበሩትን ስም ፃፉ፡፡

2. ተረቱ ምን መልእክት እንደሚያስተላልፍ ፃፉ፡፡

3. ተረቱን ጊዜና በድረጊት ቅደም ተከተል ፃፉ

ለ. የሚከተሉትን  በግዜ ቅደም ተከተል ፃፉ

1. እራት፣ ቁርስ፣ ምሳ፣ መክሰስ

2. መጎልመስ ፣መወለድ ፣መፀነስ ፣ማደግ ፣ መሸምገል

ሐ. የሚከተሉትን በድርጊት ቅደም ተከተል ፃፉ

1. መዝራት፣ ማረስ ፣ ማጨድ ፣ በጎተራ መጨመር፣ መውቃት

2. ማፍላት፣ ማጠብ፣ መውቀጥ ፣ መልቀም፣ መቁላት

3. መፀዳጃ መሄድ፣ ከእንቅልፍ መነሳት፣ ቁርስ መብላት፣ ፊትና እጅን ታጠብ ፣ ልብስ መልበስ፣ ወደ ትምህርት ቤትመሄድ

የክለሳ ጥያቄዎች

1. በድሮ ጊዜ ሰዎች ተረትን ለምን ይጠቀሙበት ነበር ?

2. ተረት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት ይተላለፋል?

3. በተረት መልእክት ማስተላለፍ ይቻላል ?

## ምዕራፍ ሰበት፡ ቤተሰብን ማገዝ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች  ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- ስለ ቤተሰብና ቤተሰብ እገዛ ምንነት ትናገራላችሁ።
- በቤተሰብ እገዛ ሰበብ የጉልበት ብዝበዛ መካሄድ እንደሌለበት ተረድታችሁ አገዛው እንዴት መካሄድ እንደለበት ትናገራላችሁ።
- የመጥበቅና መላላት ባህሪ ያላቸውን ቃላት ለይታችሁ ታነባላችሁ ትጽፋላችሁ።
- የተማሪዎች ትምህርት የሚያቋርጡበትን ምክንያት የሚያደርሰውን ጉዳት ይፅፋሉ።

ተማሪዎች በምዕራፍ ስድስት የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ እንዳጠናችሁና ከቀረበው ትምህርት ማግኘት ያላባችሁን እውቀት እንዳገኛችሁ በመተማመን አሁን ደግሞ የምዕራፍ ሰባትን ትምህርት እንቀጥላለን። በዚህም ምዕራፍ ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የምታዳብሩበትንና የቋንቋ እውቀት የምታገኙባቸው ይዘቶች ተካተው የቀረቡ ስለሆነ ጊዜ በመስጠት መስራት ይጠበቅባችኋል።

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

ከዚህ በታች የማዳመጥ ችሎታችሁን የምታዳብሩበት ምንባብ አቅርቤላችኋለሁ።ታዲያ ይህንን ምንባብ እናንተ አታነቡም። ምንባቡን የሚያነብላችሁ ሰው ፈልጉና ሲነበብ በሚገባ አዳምጡ ።ከዚያም ከምንባቡ የወጡትን የማዳመጥ ጥያቄዎች ምንባቡን ሳትመለከቱ አዳምጣችሁ ከተረዳችሁት ለመስራት ሞክሩ። ጥያቄዎቹን ሰርታችሁ ካጠናቀቃችሁ ባኋላ ምን ያህል እንደመለሳችሁ ለማመሳከር ምንባቡን ማየት ትችላላችሁ።

## ጎረቤታሞቹ

አቶ ፊጤና አቶ ሮቤራ ጎረቤታሞች ናቸው። የአቶ ፊጤ ቤተሰብ ሁለት ልጆች አላቸው። ቤተሰቡም በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የብዙ ሰውጉልበት የሚጠይቁ ወቅታዊ ስራዎች ተደራርበው ይመጡባቸዋል። የሥራዎቹብዛትና አጣዳፊነት የልጆቻቸውንም ተሳትፎ የሚፈልግበት ጊዜ አለ። አቶ ፊጤናባለቤታቸው ወይዘሮ ሌንሴ ለደቂቃ የልጆቻቸው ትምህርት እንዲቋረጥባቸው አይፈልጉም። የእርሻ ሥራቸውም እንዲስተጓጎልባቸው አያደርጉም። ጊዜያዊ ሠራተኞችን እየቀጠሩ የእርሻ ስራቸውን ስኬታማ ያደርጋሉ። ከልጆቻቸው የሚፈልጉት ነገር ቢኖር በእረፍት ጊዜያቸው አቅማቸው የሚችለውን ያህል ሥራ እንዲያግዙና በዚያውም ሥራ እንዲለምዱ ማድረግ ብቻ ነው።

አቶ ሮቤራም እንደ አቶ ፊጤ ሁሉ ልጆች አሏቸው። ለልጆቻቸው ያላቸው አመለካከትና አያያዝ ከአቶ ፊጤ ፊጽሞ የተለየ ነው። ልጆችን ስራ ማስተማርና ራሳቸውን ማስቻል ተገቢ ነው የሚል እምነት አላቸው። ጎረቤታቸው አቶ ፊጤም የሳቸውን ፈለግ ቢከተሉ ደስታቸው ነበር። ባጋጣሚ ሲገናኙም እንዲህ እያሉ ይመክሯቸዋል። "ትምህርት ትምህርት እያልክ ልጆቹን ታለፋለህ! በዚህ ዕድሜ ሥራ ለምደው፣ ቅርስ ይዘው፣ የገንዘብን ጥቅም አውቀው ካላደጉ ጥሩ አይደለም። እንዲህ የባከነውን ጊዜ መልሶ ማግኘት ስለማይቻል በጊዜ ውሳኔህን ብተቀይር ይሻላል።" ይሏቸዋል። የአቶ ሮቤራ ባለቤት ወይዘሮ ደሜ ሀሳባቸውን ደፍረው መግለጽ ባይችሉም የአቶ ፊጤን ቤተሰብ ሀሳብ ይጋራሉ። ልጅን ማስተማር ጥቅም እንዳለው ጠንቅቀው አውቀዋል።

ከስድስተኛ ክፍል ከመምህር መምሪያ የተወሰደ

መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካዳመጣችሁት ምንባብ የወጡ ናቸው አዳምጣችሁ በተረዳችሁት መሰረት በቃል መልሱ።

1. የልጆቻቸው ትምህርት እንዳይቋረጥ የሚፈልጉት ማን ናቸው?

2. ልጆቻቸው ከትምህርት ይልቅ ስራ እንዲለምዱ የገንዘብን ጥቅም አውቀው እንዲያድጉ የሚፈልጉት ማን ናቸው?

3.ልጅን ማስተማር ጥቅም እንዳለው ጠንቅቀው የሚያውቁት ማን ናቸው?

4. ጎረቤታሞቹ አባወራዎች ማንና ማን ይባላሉ?

ለ. የሚከተሉትን ሀሳቦች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት

መልሱ።

1. በአቶ ሮቤራ አመለካከት ለትምህርት የሚሰጠው ጊዜ እንደ ባከነ ነው የሚቆጠረው።

2. የአቶ ሮቤራ ልጆች ጉልበት እየተበዘበዘ ነው።

3. አቶ ፊጤ ለልጆቻቸው ትምህርት ቅድሚያ ይሰጣሉ።

4. ልጆቻቸው አቅማቸው የሚፈቅደውን ስራ በእረፍት ጊዜያቸው እንዲሰሩ የሚያደርጉት አቶ ፊጤ ናቸው ።

ሐ. ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን በቃል ተናገሩ

1. ስኬታማ

2. ይጋራሉ

3. ባጋጣሚ

4.ማስቻል

5.እንዲያግዙ

### ክፍል ሁለት መናገር

ተማሪዎች በዚህ ክፍል ትምህርታችን የመናገር ችሎታችንን ለማዳበር የሚጠቅሙን ተግባራትን እንሰራለን ፡፧ ታዲያ ካሁን በፊት እንደነገርኳችሁ ይህንን ተግባር ስንሰራ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መጠቀም የለብንም ምክንያቱም አሁን እንድናዳብር የሚፈለገው ተምህርቱን የምንማርበትን አማርኛ ቋንቋን ስለሆነ ነው።

ተግባር

ከዚህ በታች ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1. በአካባቢያችሁጉ ጉልበታቸው ያለ አግባብ ስለሚበዘበዙ ልጆች በምን ስራ ላይ ተሰማርተው እንዳሉና በልጆቹ ላይ እየደረሰ ስላለው ችግር፡፡

2. ልጆቹን ለጉልበት ብዝበዛ የዳረጋቸው ችግር ምን እንደሆነ፡፡

3. እነዚህን ልጆች እየደረሰባቸው ካለው ችግር ለማዳን ምን ምን መደረግ እንደሚኖርበት፡፡

4. አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቦቻቸውን ስራ ለመርዳት ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ሴቶች ወይስ ወንዶች? ለምን?

ከላይ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች መልሳችሁን በቅርብ ለምታገኙት ሰው ተናገሩ፡፡

### ክፍል ሶስት ማንበብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የማንበብ ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉበት ቤተሰብ ማገዝ በሚል ርዕስ ምንባብ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ ምንባቡን ለማንበብ ምቹ ቦታ ምረጡ፡፡ ሀሳባችሁን ሰብስባችሁ ልታነቡ የምትችሉበት የሚረብሻችሁ ድምፅ የሌለበት ቦታ ይሁን፡፡ ከዚያም ምንባቡን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ አንበብቡት፡፡ የምንባቡን ሀሳብ በትክክል መረዳታችሁን እርግጠኞች ስትሆኑ ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን የምትመዝኑበትን ጥያቄዎች በትእዛዙ መሰረት ስሩ፡

## ቤተሰብን ማገዝ

**የአንድ ቤተሰብ ኑሮ የተሻለ የሚሆነው ሁሉም የቤተሰብ አባል በመረዳዳት& በመተሳሰብና በመተጋገዝ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮችን ማሟላት ሲችሉ ነው፡፡ በተለይም** በዝቅተኛ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች በኑሯቸው እጅግ ይቸገራሉ፡፡ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማለትም ምግብ ልብስና መጠለያ ለማሟላት ሲቸገሩ ይታያሉ ፡፡ ኢኮኖሚያቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቤተሰቦች የግል መኖሪያ ቤት የቤት ቁሳቁስ በቂ አልባሳት የተለያ ስራዎችን የሚሰሩበት የስራ መሳሪያዎች ለምሳሌ ፡-በግብርና የሚተዳደሩ ከሆነ የእርሻ መሳሪያዎች እጥረት ሊኖርባቸው ይችላል፡፡

አንድ ቤተሰብ ከላይ የተዘረዘሩት የምግብ ፣የስራ ቁሳቁሶች፣ የቀንና የሌሊት ልብሶችና ሌሎችም ማሟላት የሚችሉት የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ተጋግዘው ሲሰሩና ለኑሮአቸው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ማፍራት ሲችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም የቤተሰብ አባላት በሚችሉት ሁሉ በስራ ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡

ቤተሰብን ለማገዝ በፕሮግራም መመራት እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ተማሪዎች በመደበኛው የትምህርት ሰዓት ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ከትምህርት ቤት መልስ ደግሞ በተዘጋጀው ፕሮግራም በመጠቀም ከአስተማሪያቸው የተሰጠውን የቤት ስራ መስራትና የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ የሚከናወኑ ስራዎችን በመስራት ቤተሰባቸውን ማገዝ ከልጆች የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

## መልመጃ አንድ

*ሀ*. ቀጥሎ የቀረቡትን ሀሳቦች በምንባብ መሰረት **እውነት** ወይም **ሐሰት** በማለት መልሱ፡፡

1. ሁሉም የቤተሰብ አባላት ተረዳድተው ከሰሩ የቤተሰቡ ኑሮ ሊሻሻል ይችላል፡፡
2. ልጆች በአባትና እናት ጥላ ስር እንክብካቤ እያገኙ ማደግ አለባቸው፡፡
3. ለልጆች የጨዋታ ጊዜን መስጠት ሥራን እንዳይለምዱ ያደርጋል ፡፡
4. ልጆች ትምህርታቸውን መማር እንጅ ስራ መስራት የለባቸውም፡፡

ለ. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ ስጡ

1. በምንባቡ መሰረት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ምን ምን ናቸው ?
2. በዝቅተኛ ኢኮኖሚ የሚኖሩ ሲል ምን ማለቱ ነው ?
3. ቤተሰብን ለመርዳት በፕሮግራም መመራት ያለብን ለምንድን ነው?
4. እናንተ ቤተሰባችሁን የምትረዱት እንዴት ነው ?

ሐ. ለሚከተሉት ቃላት የአገባብ ፍች ስጡ፡፡

1. ቁሳቁስ
2. ማሟለት
3. መተጋገዝ
4. እጥረት
5. ምክንያት

## ክፍል አራት መፃፍ

መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ የሆኑትን መልሶች በጽሑፍ ስጡ፡፡

1. የቤተሰብ መተጋገዝ ወሳኝ የሚሆነው ለምንድን ነው?
2. ተማሪዎች እንዴት ቤተሳባቸውን መርዳት ይችላሉ?
3. ተማሪዎች ትምህርታቸውን የሚያቋርጡበትን ምክንያትና የሚያስከትለውን ችግር ፃፉ፡፡

መልመጃ ሁለት

ተማሪዎች አንዳንድ ቃላት ጠብቆና ላልቶ የሚነበብ ድምፅ ሊኖራቸው ያችላል፡፤ በዚህ ምክንያት አንድ ቃል ሁለት ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡- ገና የሚለውን ቃል ብንወስድ በዚህ ቃል ውስጥ ያለው 'ና' ላልቶና ጠብቆ ሲነበብ የትርጉም ልዩነት ያመጣል ፡፡

ገና--ላልቶ ሲነበብ የገና በአልን ያመለክታል፡፡

ሀ. የሚከተሉት ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚያመጡትን የትርጉም ልዩነት በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ አስገብታችሁ አሳዩ፡፡

1. ለጋ
2. ለማ
3. ዋና
4. አያት
5. አለ

የክለሳ ጥያቄዎች

1.ቤተሰብን ለማገዝ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

2. አባዛኛውን በተሰብን በማገዝ ምክንያት ከተምህርትቤት የሚቀሩ ሴቶች ወይስ ወንዶች?

3. በአጥብቆ በማንበብና አላልቶ በማንበብ ሁለት ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ 5 ቃላትን ተናገሩ፡፡

4. ምክንያትየሚለው ቃል  መንስሌ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ወይስ ተቃራኒ ነው?

## ምዕራፍ ስምንት፡ ባህላዊ ሙዚቃ

# የሚጠበቁ ውጤቶች

## ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- የባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያ ስሞችን ትናገራላችሁ፡፡
- የባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያ ስሞችን ትፅፋላችሁ፡፡
- ያዳመጣችኋቸውን ወይም ያነበባችኋቸውን ፅሁፎች በራሳችሁ አባበል ታቀርባላችሁ፡፡
- ከቃል ሌሎች ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡
- በዐ.ነገር ውስጥ የተጓደሉ ቃላትን በመጨመር አሟልታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

ተማሪዎች በምዕራፍ ሰባት የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ እንዳጠናችሁና ከቀረበው ትምህርት ማግኘት ያላባችሁን እውቀት እንደቀሰማችሁ በማሰብ አሁን ደግሞ የምዕራፍ ስምንት ትምህርት እንቀጥላለን፡፡ በዚህም ምዕራፍ ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የምታዳብሩበትንና የቋንቋ እውቀት የምታገኙባቸው ይዘቶች ተካተው የቀረቡ ሁሌ እንደምታደርጉት ጊዜ በመስጠት መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡

### ክፍል አንድ ፡ ማዳመጥ

በዚህ ክፍል የማዳመጥ ችሎታችንን የምናዳብርበት ተግባር እንሰራለን፡፡

ተማሪዎች  በሬድዮ ወይም በቴሌቭዥን የሚተላለፍ ሙዚቃ አዳምጡ፡፡ ከዚያም

1. በሙዚቃው የተላለፈው መልእክት ስለምን እንደሆነ

2. ሙዚቃው የተጠቀማቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ

3. የሙዚቃ መሳሪያዎቹ ባህላዊ ወይስ ዘመናዊ እነዚህን ጥያቄዎች ሙዚቃውን በሚገባ ካዳመጣችሁ በኋላ  በቅርባችሁ ለምታገኙት ሰው ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር

1. ሙዚቃ ምንድን ነው?
2. በሙዚቃ ምን ምን ነገሮችን ማስተላለፍ እንችላለን፡፡
3. በአካባቢያችሁ ህብረተሰቡ ሚጠቀምባቸው ባህላዊ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ በቅርብ ለምታገኙት ሰው ተናገሩ፡፡
4. በህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን ሊሰሩ ብርብ ላሉ የቤተሰባችሁ አባለት ንገሩ፡፡
5. የምትወዷቸውን የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች ስም ተናገሩ፡፡
6. በባህላዊናበዘመናዊ ሙዚቃ መካከል ያለውን ልዩነት ግለፁ፡፡

## ክፍል ሶስት፡ ማናበብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የማንበብ ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉበት ባህላዊ ሙዚቃ በሚል ርዕስ ምንባብ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ ምንባቡን ለማንበብ ምቹ ቦታ መምረጥ ይጠበቅባችኋል፡፡ ሀሳባችሁን ሰብስባችሁ ልታነቡ የምትችሉበት የሚረብሻችሁ ድምፅ የሌለበት ቦታ ይሁን፡፡ ከዚያም ምንባቡን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ አንበብቡት፡፡ የምንባቡን ሀሳብ በትክክል መረዳታችሁን እርግጠኞች ስትሆኑ ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን የምትመዝኑበትን ጥያቄዎች በትእዛዙ መሰረት ስሩ፡፡

## ባህላዊ ሙዚቃ

በሀገራችን የተለያዩ በህላዊ ሙዚቃዎች ሲኖሩ እነርሱም ከክልል ክልል ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የኦሮሚያ ክልል ህዝቦች ባህላዊ ሙዚቃ ከአማራ ክልል ህዝቦች ባህላዊ ሙዚቃ ይለያል፡፡

ባህላዊ ሙዚቃ የሚከናወነው በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ነው፡፡ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት በአካባቢ ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች የሚሰሩ እንደ ክራር፣ መሰንቆ ፣ከበሮ ፣ዋሽንት ፣በገና ፣ፅናፅል እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በኦሮሚያ ክልል አብዛኛውን ጊዜ ለባህላዊ ሙዚቃ የምንጠቀምባቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ማሲንቆና ክራር ሲሆኑ ሁለቱም የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

እነዚህ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከአካባቢያችን ሊገኙ ከሚችሉ ጥሬ እቃዎች በቀላል ዘዴና በአጭር ጊዜአት ውስጥ ሊሰሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

ማሲንቆና ክራርን ለመስራት የሚያገለግሉ ጥሬ እቃዎች የፍየል ወይም የሚዳቆ ቆዳ የተለያዩ መጠን ያላቸው እንጨቶች፣ የፈረስ ጭራ፣አነስተኛ ገበቴ፣ኮፐርሳቶ እንጨት፣ቺንጋ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም መስራትና መጠቀም ይቻላል።

መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት ምንባብ  መሰረት መልሱ።

1. በህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?
2. በኦሮሚያ ክልል በስፋት የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው?
3. ማሲንቆና ክራር ለመስራት የምንገለገልባቸውን ጥሬ እቃዎች ዘርዝሩ።

ለ. የሚከተሉትን ሀሳቦች  በምንባብ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ

1. ባህላዊ ሙዚቃ በሁሉም ክልል ተመሳሳይ ነው።
2. ከበሮና በገናም ከባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ይመደባሉ።
3. ማሲንቆና ክራር ሁለቱም የክር መሳሪያዎች በመባል ይታወቃሉ።
4. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ከአካባቢ በሚገኙ ጥሬ እቃዎች ሊሰሩ ይችላሉ፡

ሐ. ከላይ የቀረበውን ምንባብ በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን ይሰራሉ?
2. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉትን ዘርዝራችሁ ፃፉ።
3. በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ፃፉ፡

## ክፍል አራት፡ መፃፍ

መልመጃ አንድ

ሀ. ከተሰጡት ቃላት ፊደሎቹን ቦታ በማቀያር ሌሎች ቃላትን መስርቱ

ምሳሌ፡-መስከረም-- ከረመ፣መከረ፣ስም፣

1. ማርጠብ
2. አገልግሎት
3. ተበሳጨ

4. አጠራቀመ
5. አስመጣ

ለ. በአረፍተ ነገር ውስጥ የተጓደሉትን ቃላት ከተሰጡት ቃላት በመምረጥ ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ፡፡

ክር ፍየል ሙዚቃ ባህል

1. ባህላዊ የ---------------መሳሪያዎች ከአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች ይሰራሉ፡፡
2. ለባህላዊ -------------- ባህላዊ መሳሪያ ያስፈልጋል፡፡
3. ለክራር መስሪያ የ-------------- ቆዳ እንጠቀማለን፡፡
4. ክራርና ከበሮ የ--------------ማሳሪያዎች ይባላሉ፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የምንላቸው ምን ምን ናቸው

2. ባህሳዊ የሙዚቃ መሳሪያ ከዘመናዊ የሙዚቃ መሳያ በምን ይለያል

3. በኦሮሞ ባህላዊ ሙዛቃዎች ውስጥ አብዛኛውን ግዜ የማንጠቀመው የሙዚቃምን ምን በመባል ይታወቃሉ

4. ክራርና ማሲንቆ ከምን ከምን ሊሰሩ ይችላሉ

## ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ወፎች

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- በአካባቢያችሁ ስለሚኖሩ ወፎች አኗኗር፤ ጥቅምና ጉዳት ታብራራላችሁ፡፡
- ስለወፎች ጥቅምና ጉዳት ታነባላችሁ፤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ቃላትን ገጣጥማችሁ ዐረፍተ ነገር ትመሠርታላችሁ፡፡
- ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ድርብ ቃላትን ትመሠርታላችሁ፡፡
- የተለያዩ የወፍ ሥዕሎችን በማየት ስማቸውን ትጽፋላችሁ፡፡

ተማሪዎች በምዕራፍ ስምንት የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ እንዳጠናችሁና ከቀረበው ትምህርት ማግኘት ያላባችሁን እውቀት እንደቀሰማችሁ እተማመናለሁ፡፡ አሁን ደግሞ የምዕራፍ ዘጠኝ ትምህርታችንን እንቀጥላለን፡፡ በዚህም ምዕራፍ ውስጥ ልክ እንደሌሎቹ ምዕራፍ ትምህርቶች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የምታዳብሩበትንና የቋንቋ እውቀት የምታገኙባቸው ይዘቶች ተካተው የቀረቡ ሲሆን ሁሌ እንደምታደርጉት ጊዜ በመስጠት መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡

### ክፍል አንድ፡መናገር

ተማሪዎች አሁን የመናገር ችሎታችንን ልናዳብር የምንችልበትን ተግባር እንሰራለን፡፡ ታዲያ ካሁን በፊት የነገርኳችሁን ጉዳይ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ፡፡ በተቻለ መጠን ይህንን ተግባር ስንሰራ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም ተግባሩን የምንሰራው በአማርኛ ቋንቋ የመናገርችሎታችንን ለማዳበር ስለሆነ ነው፡፡

ተግባር

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ወፎች ስም ተናገሩ
2. ወፎች የት ይኖራሉ?
3. ወፎች እንዴት ነው የሚራቡት?
4. የሁሉም ወፎች ዝርያ አንድ አይነት ነው? ለምን?
5. ከወፍ ዝርያዎች ውስጥ አጥቢ የሆነችው ምን ትባላላች?

## ክፍል ሁለት ማንበብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የማንበብ ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉበት ወፎች በሚል ርዕስ ምንባብ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ ምንባቡን ለማንበብ ምቹ ቦታ መምረጥ ይጠበቅባችኋል፡፡ ሀሳባችሁን ሰብስባችሁ ልታነቡ የምትችሉበት የሚረብሻችሁ ድምፅ የሌለበት ቦታ ይሁን፡፡ ከዚያም ምንባቡን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ አንበብቡት፡፡ የምንባቡን ሀሳብ በትክክል መረዳታችሁን እርግጠኞች ስትሆኑ ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን የምትመዝኑበትን ጥያቄዎች በትእዛዙ መሰረት ስሩ፡፡

### ወፎች

ወፎች የሚለው ስያሜ ክንፍና ላባ ያላቸውን የወፍና የአሞራ ዝርያዎችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ፡-ከአሞራዎች እንደ ንስር ጭልፊትና ቅልጥም ሰባሪ ያሉት ሊጠቀሱ ሲችሉ ከወፍ ወገን ደግሞ ዲንቢጥ የመስቀል ወፍ ጨረባና ግሪሳ ጥቂቶቹ ናቸው ፡፡ በአለም ላይ ወደ ዘጠን ሺህ የሚጠጉ የወፍ ዝርያዎች ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል፡ ወፎች የተለያ የአየር ንብረቶች ባሏቸው የምድር እርከኖች ሁሉ ይኖራሉ፡፡ በነዚህ በተለያ የምድር ክልሎች በየግዜው ከሚለዋወጠው የአየር ጠባይ ለማምለጥና ህይወታቸውንም ለማትረፍ እየተሰደዱና እየፈለሱ ረጅም ርቀት በመብረር አመቺ የአየር ንብረት ባለው አካባቢ ይከርሙና የአየሩ ሁኔታ ሲሻሻል ወደ ቀድሞው ስፍራቸው ይመለሳሉ፡፡ ይህ በደመነፍስ ለወፎች ተፈጥሮ የለገሰቻቸው ችሎታ ነው፡፡

ወፎች ከመሰሎቻቸው ጋር መግባባት የሚያስላቸው ከፍተኛ የመግባባት ችሎታ አላቸው፡፡ ለመግባቢያነት የሚጠቀሙትም የተለያዩ ሙዚቃዊ ቃና ያላቸው ድምጾችን ነው፡፡

አብዛኞዎቹ ወፎች የሚራቡት እንቁላል በመጣል ነው፡፡ ለመራባት ደግሞ ግንኙነት ይፈጽማሉ፡፡ ሴቴ ወፎች እንቁላል ይጥላሉ፡፡ እንቁላላቸውንም በመታቀፍ ሙቀት እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንድ የወፍ ዝሪያዎች እንቁላሎቻቸውን ወንዴው እና ሴቷ ወፍ ተራ በተራ ይታቀፋሉ፡፡ ከዚያም ቀኑ ሲደርስ ይፈለፈሉና ጫጩቶች ከእንቁላሎቹ ውስጥ ይወጣሉ፡፡ በተጨማሪም ጫጩቶቹ አድገው ራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ ወንዴ ወፍ እና ሴቷ ወፍ ተራ በተራ ይመግባሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ጫጩቶቹን በመንከባከብ ከጠላቶቻቸውም ይጠብቃሉ፡፡ የወፎች የሕይወት ዑደትም በዚህ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡

**መልመጃ አንድ**

ሀ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልሶችን በጽሑፍ ስጡ፡፡

1. ወፎች የሚመደቡት ከየትኞቹ እንስሳት ውስጥ ነው?
2. ወፎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱት እንዴት ነው?
3. በምንባቡ መሠረት ወፎች እንዴት ነው ሚራቡት ?
4. ወፎች ከመሰሎቻቸው ጋር እንዴት ይግባባሉ፡፡

ለ. ባነበባችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አብዛኛዎቹ ወፎች የሚራቡት እንቁላል በመጣል ነው፡፡
2. ማንኛውም ወፍ ከአንዱ ሠፈር ወደ ሌላ ሠፈር ይበራሉ እንጂ የአገሮችን ድንበር በማቋረጥ ሩቅ መብረር አይችሉም፡፡
3. ሁሉም የወፍ ዘሮች ክንፍ አላቸው፡፡
4. የተወሰኑት ወፎች ክንፍ እንጂ እግር የላቸውም፡፡
5. ወፎች እርስ በርሳቸው መግባባት የሚያስችላቸው ከፍተኛ የቋንቋ ችሎታ አላቸው፡፡
6. ጫጩቶችን የመመገብና የመንከባከብ ኃላፊነት የሴቴ ወፎች ብቻ ነው፡፡

**መልመጃ ሁለት**

**1. በ"ሀ" ረድፍ ሥር ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ፍች ሊሆኑ የሚችሉትን በ"ለ" ረድፍ ሥር ከቀረቡት ውስጥ በመምረጥ አዛምዱ።**

| "ሀ" | ለ" |
|---|---|
| -------------- 1. አካል | ሀ. ልክ |
| -------------2. መዋኘት | ለ. ይከፈላሉ |
| -------------3. መጠን | ሐ. መሰሎቻቸው |
| -------------4. ባህሪይ | መ. በውኃ ላይ መንሳፈፍ |
| -------------5. አቋርጠው | ሠ. ሰውነት |
| -------------6. በጣም ትናንሽ | ረ. ፀባይ |
| -------------7. ዝሪያዎቻቸው | ሰ. ተሻግረው |
| -------------8. መራባት | ሸ. ዙረት (ሽክርክር) |
| -------------9. ይመደባሉ | ቀ. መባዛት |
| -------------10. ኡደት | በ. ጥቃቂን |

### ክፍል ሶስት ፡ መፃፍ

**መልመጃ አንድ**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ወፎች ዓይነትና የሚኖሩበትን አካባቢ ጻፉ።
2. የወፎችን አኗኗር ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ጻፉና ።
3. ወፎች ለሰው ልጆች የሚሰጡትን ጥቅሞች ጻፉ።

**መልመጃ ሁለት**

**ቀጥሎ የቀረቡትን  የወፎች ሥዕል ተመልከቱና መጠሪያቸውን ጻፉ።**





----------------------------------                ---------------------------------

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. . ቀጥሎ የቀረቡትን የተዘበራረቁ ቃላት አስተካክሉና የተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን ጻፉ።**

ምሳሌ፦

ለሰው፤ ጥቅሞችን፤ ይሠጣሉ፤ ወፎች፤በርካታ፤ ልጆች። (የተዘበራረቁ ቃላት)

ወፎች ለሰው ልጆች በርካታ ጥቅሞችን ይሠጣሉ። (የተስተካከለ ዐረፍተ ነገር)

1. ወፎች፤ ረጅም፤ ሲኖሩ፤ ደግሞ፤ ዕድሜ፤ አጭር፤ አንዳንድ፤ ዕድሜ፤ ይኖራሉ፤ አንዳንዶች።
2. በሰብል፤ ላይ፤ ጊሪሳ፤ ምርት፤ ወፎች፤ ጉዳት፤ ከፍተኛ፤ ያደርሳሉ።
3. ፓሮት፤ ንግግር፤ መልሶ፤ የሚባለው፤ የሰውን፤ ወፍ፤ ይናገራል፤ ኮርጆ።
4. የወፍ፤ የተለያዩ፡ ለመኖሪያነት፤ ዝሪያዎች፤ አካባቢዎችን፤ ይመርጣሉ፤ የተለያዩ።
5. ወፎች፤ በክረምት፤ ወራት፤ አንዳንድ፤ አካባቢዎች፤ ለቅቀው፤ አካባቢያቸውን፤ ሩቅ፤ በመሄድ፤ወደ፤ይሰደዳሉ።

**ለ. ቀጥሎ የተሰጡትን ጥንድ ቃላት በማጣመር ድርብ ቃላትን መሥርቱ፡፡**

ምሳሌ፡ - 1. "ቃለ ጉባኤ" የሚለው ድርብ ቃል የተመሠረተው "ቃል" እና "ጉባኤ" ከሚሉት ሁለት ቃላት ነው፡፡

2. "መዝገበ ቃላት" የሚለው ድርብ ቃል ደግሞ የተመሠረተው "መዝገብ" "ቃላት" ከሚሉት ሁለት ቃላት ነው፡

**በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ቀጥሎ ከቀረቡት ጥንድ ቃላት አንድ ጥምር ቃል መሥርቱ፡፡**

1. ቤት እና መጽሐፍ ----------------------------------

2 .ፀር እና ተባይ ----------------------------------

3. ቃል እና መጠይቅ ----------------------------------

4. ፀር እና አረም ----------------------------------

5. .ልብ እና ወለድ ----------------------------------

6. አይን እና አፋር ----------------------------------

7. አቅም እና ቢስ ----------------------------------

8. .ኃይል እና መለኮት ----------------------------------

9. ከርስ እና ምድር ---------------------------------

10. ልብ እና ቢስ--------------------------------------

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ወፎች ከየትኞቹ የእንስሳት አይነት ይመደባሉ?
2. የወፎች ላባ ለምን ይጠቅማቸዋል?
3. ወፎች ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት እንዴት ነው?
4. አብዛኛዎቹ ወፎች የሚራቡት እንዴት ነው?
5. አብዛኛዎቹ ወፎች ከመሰሎቻቸው ጋር እንዴት ይግባባሉ?

## ምዕራፍ አስር ፡ መረጃ ማግኘት

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኂላ፡፡

- የመረጃ ምንጮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ስዕሎችን ተመልክታችሁድርጊቱን ትናገራላችሁ፡፡
- ስዕሎችን ተመልክታችሁ  የግርጌ መግለጫ ትሰጣላችሁ፡፡
- ከመረጃ ያገኙትን ሀሳብ በመፃፍ  በንግግር ትገልፃላችሁ፡
- ስሞችን በነጠላና በብዙ ቁጥር ትፅፋላችሁ፡፡
- የተለያዩ መደብ አመልካች ቃላትን በማስገባት ዓረፍተ ነገር ትፅፋላችኍ፡፡
- የቃልን እርባታዎች ፅፋችሁ  ታነባለችሁ፡፡
- ምንባብ አንብበው ፍሬ ሃሳቡን ትረዳላችሁ ፡፡

ተማሪዎች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ እንዳጠናችሁና ከቀረበው ትምህርት ማግኘት ያላባችሁን እውቀት እንደቀሰማችሁ እተማመናለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ለዚህ የክፍል ደረጃ የመጨረሻ የሆነውን የምዕራፍ አስር ትምህርታችንን እንቀጥላለን፡፡ በዚህም ምዕራፍ ውስጥ  ልክ እንደሌሎቹ ምዕራፍ ትምህርቶች አራቱን የቋንቋ ከሂሎች የምታዳብሩበትንና የቋንቋ እውቀት የምታገኙባቸው ይዘቶች ተካተው የቀረቡ ሲሆን ሁሌ እንደምታደርጉት ጊዜ በመስጠት መስራት ይኖርባችኂል፡፡

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

ተግባር 1

ተማሪዎች መረጃ ምንድን ነው? መረጃከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የሚገኝ ስለ አንድ የተፈጠረ ነገር ወይም ሊፈጠር ስላለ ነግር የሚገልፅ ሚያሳውቅ ነው አላችሁ! በጣም ጥሩ እስኪ አሁን የማዳመጥ ችሎታችንን ለማሳደግ እንዲረዳን ሬድዮ አዳምጠን  ወይም ቴሌቭዥን ተመለክተንና አዳምጠን ያገኘነውን መረጃ በቅርብ ለምናገኘው ሰው እንናገር፡፡

ተግባር 2

ከቤተሰባችሁአንጋፋ የሆነ ሰው ምረጡና እንዲህ እንደዛሬው በአለም አቀፍ ደረጃተከስቶ ስለነበረው በሀገራችን የህዳር በሽታ ተብሎስለተሰየመው ተላላፊ በሽታ ጠይቁና መረጃ ሰብስቡ

ጥያቄያችሁ

1. መቼ እንደተከሰተ

2. ያደረሰውን ጉዳት

3. በምን እንደተከላከሉት

## ክፍል ሁለት ፡ መናገር

ከዚህ በመቀጠል ያቀረብኩላችሁን ስዕሎች ተመልክታችሁ ድርጊቱን በቅርባችሁ ላለ ሰው ተናገሩ፡፡

1



2



3.



## ክፍል ሶስት፡ ማንበብ

ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የማንበብ ችሎታችሁን ልታዳብሩ የምትችሉበት መረጃ ማግኘት በሚል ርዕስ ምንባብ አቅርቤላችኂለሁ። ምንባቡን ለማንበብ ዘወትር እንደምታደርጉት ምቹ ቦታ መምረጥ ይጠበቅባችኂል። ከዚያም ምንባቡን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ አንብቡት። የምንባቡን ሀሳብ በትክክል መረዳታችሁን እርግጠኞች ስትሆኑ ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን የምትመዝኑበትን ጥያቄዎች በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

### መረጃ ማግኘት

መረጃ ማለት ከአሁን በፊት ምን እንደተሰራ ፣አሁን ምን በመሰራት ላይ እንዳለና ለወደፊት ምን እንደታቀደ ለማወቅ የሚረዳ መሳሪያ ነው። መረጃ በተለያዩ መንገዶች ሊገኝ ይችላል። ቤተ-መጻህፍትና ቤተ-ሙከራ ዋና ዋናዎቹ የመረጃ መገኛዎች ናቸው።ጽሁፎችን በቤተመጻህፍት ተገኝቶ ወይም የሚነበበው ጽሁፍ በተገኘበት በማንበብ ( ጥናታዊ ጽሁፎችን፣ መጽሀፎችን፣ መጽሄቶችን፣ ጋዜጦችን፣ በራሪ ጽሁፎችን ወዘተ. በማንበብ) ኩነቶችን፣ ስዕሎችንና ሌሎች ነገሮችን በአካል ተገኝቶ በመመልከት፣ ስለጉዳዮች ከሰዎች በመስማት፣ መገናኛ ብዙሃንን በመከታተል (ቴሌቪዥን፣ ሬድዮ ወዘተ. በመከታተል) ኢንተርኔትና የመሳሰሉትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም ሊገኝ መረጀ ይችላል።

መረጃ የተለያ ጥቅሞችን ይሰጠናል። ለምሰሌ የነገሮችን አጀማመር፣አካሄድና የመጨረሻ ውጤት ለማወቅ፣ የችግሮችን ምንጭ ለማወቅና ዘለቄታዊ መፍትሄ ለመስጠት፣የሰዎችን ተግባር የተቀላጠፈ ለማድረግ፣ የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውጤታማ ለማድረግ፣የተሸሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመጠቀም፣ ወዘተ ያግዛል።

መረጃ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት ሁሉ በጥንቃቄና በትክክል ካልተላለፈና ካልተወሰደ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ይኖረዋል። ለምሳሌ፡- በደንገተኛ እሳት አደጋ ምክንያት  በአንድ አካባቢ የደረሰውን ጉዳት በትክክል ያለማስተላለፍ በአካባቢው ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች በመንግስትም ሆነ በበጎ አድራጊ ድርጆቶች እንዲሁም በተለያ ግለሰቦች  በቂ ድጋፍ እንዳይደረግላቸው ያደርጋል።

መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ

1. መረጃ ምንድን ነው?
2. መረጃ ከምን ከምን ከምን ማግኘት ይቻላል?
3. መረጃ ምን ምን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል?
4. መረጃ ጉዳት ሊኖረው ይችላል? መሰለሳችሁ አዎ ከሆነ እንዴት?
5. ለአራተኛው ጥያቄ መልሳችሁ አይኖረውም ከሆነ ምክንያታችሁን ግለፁ።

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።

1. መረጃ የተሰራን፣ በመሰራት ላይ ያለንና ወደፊት ስለሚሰሩ ነገሮች ፍንጭ ይሰጠናል።

2. ኢንተርኔት በመጠቀም  የምንገኛቸው  መረጃዎች ሁልግዜ ትክክል ናቸው፡፡
3. መረጃ የማህበረሰብን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለተካዊ ጉዳዮችን ውጤታማ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
4. መረጃ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡
5. መረጃን ከሚነበቡ መፃህፍት፣ከበራሪ ወረቀቶች & ከሬድዮና ከቴሌቭዥን ማግኘት እንችላለን፡፡
6. በመረጃ ስህተት ሀገር የሚጎዱ ነገሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

ክፍል አራት፡ መፃፍ

ሥዕሎቹን በመመልከት የግርጌ መግለጫ ጻፉላቸው፡፡ምሳሌ፡-



ገበሬው በሬዎቹን ጠምዶ እያረሰ ነው ፡፡

1.




2



------------------------------------------  ------------------------------------------

## ክፍል አምስት፡ ሰዋሰው

### መልመጃ አንድ

**ሀ. በነጠላ ቁጥር የቀረቡትን ስሞች በብዙ ቁጥር ጻፏቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ወንበር --ወንበሮች

በግ --በጎች

1. ጫማ ---------------------
2. ሰው --------------------
3. እርሳስ --------------------
4. ኳስ ---------------------
5. መኪና ---------------------
6. ተማሪ-------------------
7. ወፍ---------------------
8. ዛፍ----------------------
9. ፖሊስ------------------
10. ልብስ——————

**ለ. በብዙ ቁጥር የቀረቡ ስሞችን በነጠላ ቁጥር ጻፏቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ፍየሎች -- ፍየል

ወንበሮች -----ወንበር

1. ደብተሮች --------------------------
2. ሱቆች ----------------------------
3. ቤቶች -------------------------- ----
4. ልጆች --------------------------
5. ግመሎች ----------------------------
6. ብሮች----------------------
7. ቁጥሮች---------------------
8. ሰዓቶች---------------------
9. ጠርሙሶች-----------------
10. ድመቶች------------------

## ሐ.ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት ስሯቸው፡፡

| መነሻ ቃል | ከመነሻ ቃል የተመሰረቱ ቃላት | | | |
|---|---|---|---|---|
| መጣ | መምጣት | አመጣጥ | መምጫ | መጪ |
| ሄደ | | | | |
| ሰጠ | | | | |
| ሰራ | | | | |
| ለበሰ | | | | |
| አነበበ | | | | |

**መ. ከታች የቀረቡ ቃላትን በተሰጣችሁ ክፍት ቦታ ሙሉ፡፡**

**እኔ እኛ**

**አንተ አንቺ እናንተ**

**እርሷ እርሱ እነእርሱ**

1. ኳሱን ገዝቶ ለ---------------------- ሰጣችሁ፡፡

2. ገንዘቡን የወሰደው--------------------- ነው፡፡

3. ቡና ገዝተሽ እንድትመጪ ነግሬሽ የነበረ ---------------- ግን ሳትገዥ መጣሽ፡፡

4. ለ------------- ኳስ ተገዝቶልናል፡፡

5. ---------------- የሚሄዱት  ነገ ነው፡፡

6. ከ----------- ጋር መስራት ትፈልጊያለሽ?

7. ጥሩ ባህርይ ካላቸው ሰዎች አንዱ --------------ነህ፡፡

8. በማራቶን ሩጫ አሸናፊ የሆነችው ---------------- ናት፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. መረጃ ምንድን ነው?

2. የመረጃ ምንጮች ምን ምንድን ናቸው ?

3. መረጃ ምን ጥቅም ያስገኛል?

## ዋቢ መፃህፍት

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስድስተኛ ክፍል የተማሪ መፀሀፍ 2011 እትም

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስድስተኛ ክፍል የመምህር መምሪያ መፀሀፍ 2011 እትም

## ከምዕራፎቹ ለተመረጡ መልመጃዎች ናሙና መልሶች

### ምዕራፍ ስድስት

### ክፍል ሶስት

መልመጃ አንድ

ሀ. 1. የአይጥን ልጅ አገባለሁ በሚል ሰበብ

2. አይጥ

3. አታሎ ሊበላቸው

ለ.1 ሀሰት

2. ሀሰት

3. እውነት

4.ሀሰት

መልመጃ ሁለት

1. መቆፈር

2..መወያየት

3. አብሮነት

4. ማሞኘት/ማጭበርበር

5. መጉዳት

### ክፍል አራት

ሀ.1. አጥይና ድመት

2. ድመት አይጥን አታሎ ሊበላ መፈለጉን

3. በመጀመሪያ ድመት ከአይት መዛመድ እፈልጋለሁ አለ

በመቀጠል የአይጥን ልጀ ለማግባት አማላጅ በመላክ ካይጥ ቤተሶች ጋር ተስማማ

በሶስተኛ ደረጃ አንድ አይጥ ከሌሎች አይጦችጋር ተማክራ ጉድጓድ ቆፈሩ

ሙስራው ድመት ሆ እንቅ እንቅ እያለ ወደ አይቶች ቤት ባጅብ መጣ

አይጦችም እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል በማለት በየጉድጓዳቸው ገብተው አመለጡ

ለ. 1. ቁርስ፣ ምሳ፣ መክሰስ፣ እራት

2. መፀነስ፣ መወለድ፣ ማደግ፣ መጎልመስ ፣መሸምገል

ሐ. 1. መረስ፣ መዝራት፣ ማረም ፣ ማጨድ ፣ መውቃት ፣በጉተራ ማስገባት

2. መልቀም ማጠብ መቁላት መውቀጥ ማፍላት

3፣ ከእንቅልፍ መነሳት፣ መፃዳጃ ቤት መሄድ፣ ፊትና እጅን መታጠብ፣ ልብስ መቀየር፣ ቁርስ መብላት ፣ወደ ትምህርት ቤት መሄድ

## ምዕራፍ ሰባት

## ክፍል አንድ

መልመጃ አንድ

ሀ.1. አቶ ፊጤ

2. አቶ ሮቤራ

3. አቶ ፊጤና ባለቤታቸው

4. አቶ ፊጤና አቶ ሮቤራ

ለ. 1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት

ሐ. 1. ውጤታማ
2. ይደግፋሉ
3. ሳይታሰብ
4. ማብቃት/እንዲችሉ ማድረግ
5.እንዲረዱ

## ክፍል ሶስት

ሀ. 1. እውነት
2. እውነት
3. ሀሰት
4.ሀሰት

ለ. 1 ምግብና መጠጥ ልብስ መጠለያ

2. በቂ መተዳደሪያ የሌላቸው

3. ጊዜያችንን በአግባቡ ለመጠቀም

4. የተለያ መልስ ሊሆን ይችላል

ሐ. 1. መሳሪያዎች/እቃዎች

2. እንዲያገኙ ማድረግ

3. መረዳዳት

4. እጦት/በቂ አለመሆን

5.ሰበብ/ መንስኤ

**ክፍል አራት**

መልመጃ አንድና ሁለት የተያዩ መልሶች ለሆኑ ይችላሉ።

**ምዕራፍ ስምንት**

**ክፍል ሶስት**

**መልመጃ አንድ**

ሀ. 1. ከበሮ፣ ማሲንቆ ፣ክራር፣ በገና፣ ዋሽንት

2. ማሲንቆና ክራር

3. እንጨት፣ የፈረስ ጭራ ፣የጎማ ክር፣ ትንንሽ ገበቴዎች፣ የእንስሳት ቆዳ

ለ. 1. ሀሰት

2. እውነት

3. እውነት

4. እውነት

ሐ. 1. በአካባቢ ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች

2. ከበሮ፣ ማሲንቆ ፣ ክራር ፣ ዋሽንት፣ በገና

3. እንደየ አካባቢው ሊለያይ ይችላል።

## ክፍል አራት

ሀ. 1. ማር፣ መብ፣ ማጠብ ፣ ጠማ

4. አጠራ፣ ራቀ፣ ጠራ፣ ቀራ

2. ገል ፣ ግሎ፣ አብል ፣ ገልሎት

5. መጣ፣ ስመጣ፣ አስጣ ፣ አመጣ

3. በሳ ተበሳ

ለ. 1. ሙዚቃ

3. ፍየል

2. ሙዚቃ

4. ባህል

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ክፍል ሁለት

መልመጃ አንድ

ሀ. 1. ክንፍና ላባ ካላቸው /ከአእዋፋት /

2. በመብረር

3. አብዛኛዎቹ እንቁላል በመጣል

4. በድምፅ

ለ. 1. እውነት

2. ሀሰት

3. እውነት

4. ሀሰት

5. ሀሰት

6. ሀሰት

መልመጃ ሁለት

1. ሠ

2.መ

3.ሀ

4.ረ

5. ሰ

6. በ

7. ሐ

8.ቀ

9. ለ

10.ሸ

## ክፍል ሶስት

መልመጃ ሁለት

1. የሌሊት ወፍ

2. ሰጎን

መልመጃ ሶስት

ሀ.

1. አንዳንድ ወፎች ረዥም እድሜ ሲኖሩ አነዳንዶቹ ደግሞ አጭር እድሜ ይኖራሉ፡፡

2. ግሪሳ ወፎች በሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

3. ፓሮት የሚባለው ወፍ የሰውን ንግግር ኮርጆመልሶ ይናገራል፡፡

4.የተለያዩ የወፍ ዝርያዎች ለመኖሪያነት የተለያዩ አካባቢዎችን ይመርጣሉ፡፡

5. አንዳንድ ወፎች በክረምት ወራት አካባቢያቸውን ለቀው በመሄድ ወደ ሌላ አካባቢ ይሰደዳሉ፡፡

ለ. 1. ቤተ-መጽሐፍ
2. ፀረ-ተባይ
3. ቃለ-መጠይቅ
4. ፀረ-አረም
5. ልብ-ወለድ
6. አይነ-አፋር
7. አቅመ-ቢስ
8.ሀይለ-መለኮት
9. ከርሰ-ምድር
10. ልበ-ቢስ

## ምዕራፍ አስር

## ክፍል ሶስት

መልመጃ አንድ

ሀ. 1-5 በምንባቡ መሰረት ይመለሳሉ

ለ. 1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. እውነት

## ክፍል አራት

1. ሴት ሯጮች በውድድር ላይ ናቸው ፡፡

2. መምህሩ ተማሪዎቻቸውን እያስተማሩ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

ሀ.1 ጫማዎች 6. ተማሪዎች

2. ሰዎች 7. ወፎች

3. እርሳሶች 8.ዛፎች

4. ኳሶች 9. ፖሊሶች

5. መኪናዎች 10. ልብሶች

ለ. 1. ደብተር 6. ብር

2. ሱቅ 7. ቁጥር

3. ቤት 8. ሰዓት

4. ልጅ 9. ጠርሙስ

5.ግመል 10. ድመት

**ሐ.ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት ስሯቸው።**

| መነሻ ቃል | ከመነሻ ቃል የተመሰረቱ ቃላት | | | |
|---|---|---|---|---|
| መጣ | መምጣት | አመጣጥ | መምጫ | መጪ |
| ሄደ | መሄድ | አካሄድ | መሄጃ | ሂያጅ |
| ሰጠ | መስጠት | አሰጣጥ | መስጫ | ሰጪ |
| ሰራ | መስራት | አሰራር | መስሪያ | ሰሪ |
| ለበሰ | መልበስ | አለባበስ | መልበሻ | ለባሽ |
| አነበበ | ማንበብ | አነባበብ | ማንበብቢያ | አንባቢ |

መ. 1. እርሷ 4. እኛ 6. እኛ፣ እኔ፣ እነርሱ ፣ እርሱ፣እርሷ

2. እሱ 5. እነርሱ 7. አንተ

3. አንቺ 8. እርሷ